# "ወንድማማች ሕዝቦች"

## የኢትዮጵያን ሕዝቦች ታሪካዊ ትስስር ለማጠናከር
## የተቋቋመ የሲቪክ ድርጅት

### መግቢያ

ይህ "ወንድማማች ሕዝቦች" በሚል ስያሜ በመቋቋም ላይ የሚገኘው የሲቪክ ድርጅት ሀገራችን አሁን ያለችበትን ሁኔታ በማጤንና በቅርብም ሆነ በሩቅ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች ያለፉባቸውንና የሚገኙባቸውን ተመክሮዎች በማገናዘብ ወቅታዊነቱ ታምኖበት ከተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔር/ብሔረሰቦች የተውጣጡ ኢትዮጵያዊያን ተቀራርበው በመነጋገርና በመመካከር የመሠረቱት ነው::

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች የተውጣጡ ወደ 55 ሚሊዮን የሚጠጉ ሕዝቦች የሚኖሩባትና ከ100 በላይ ልዩ ልዩ ቋንቋዎችና ልሳኖች (dialects) የሚነገሩባት በአፍሪቃ ቀንድ አማካይ ስፍራ የያዘች ባለታሪክ ሀገር ነች:: ጂአግራፊያዊ አቀማመጧ: የሕዝቦቿ ታሪክና ባህል: ተፈጥሮአዊ ሥሪቷና የነዋሪዎቿ መልክአምድራዊ አሰፋፈር የተለያዩ ገጽታዎችን የመላበሱን ያህል ከእነዚህ ልዩነቶች ባሻገር የታሪክና የባህል መወራረሶችን: ተቀራራቢነቶችንና ተመሣሣይነትን በሚያንፀባርቁ አያሌ ሁነቶችና ታሪካዊ ክንውኖች ውስጥ ከሞላ ጎደል በሙሉ የጋራ ተመክሮን ያሳለፉ ህዝቦች ሀገር ነች::

የኢትዮጵያ ህዝቦች ባሳለፉቸው የረዥም ዓመታት ፖለቲካዊ: ባህላዊ: ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የህይወት ገጽታዎች ውስጥ ከተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች በየዘመኑ በክልልም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ በመንበረ ሥልጣን የተፈራረቁ ገዥዎች ሲጭኑባቸው የቆዩትን የአገዛዝ ቀንበር ለመስበር በየአካባቢው የተናጠል ተጋድሎዎችን ከማድረጋቸው ባሻገር ከቅርብም ሆነ ከሩቅ እየተነሱ ለባርነት የተመኟቸውን የውጭ ወራሪዎች በህብረት የተቋቋሙባቸው ታሪካዊ ወቅቶች በርካታ ናቸው:: ስለዚህም ግንኙነቶቻቸው የጠብና የሽኩቻ የነበረ የመሆኑን ያህል የመቀራረብና የመፋቀር እንዲሁም ለጋራ ዓላማ በህብረት እጅ ለእጅ ተያይዘ ለነፃነትና ለክብር አብሮ የመዋደቅም ጭምር ነበር::

ምንም እንኳን ሥልጣን ለመያዝና በኋላም የአገዛዝ ዘመንን ለማራዘም በአፄዎች፡ በጦር አበጋዞች፡ በጉልተኛ የአካባቢ መሣፍንትና የገዥ መደቦች አማካይነት ልዩነቶችን በማጋነንና የእርስ በእርስ ጥላቻን በማካረር ላይ የተመረኮዙ የማለያየትና የማራራቅ ሙከራዎች በተደጋጋሚ ሲከሰቱ የቆዩ ቢሆንም እነዚህ አፍራሽ ተጽዕኖዎች በዘላቂነት በህዝቦች ሥነ ልቡና ውስጥ ሊሠርፁና ቋሚ ስፍራ ለመያዝ ከቶ አልተቻላቸውም:: ለዚህም ነው በኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ ውስጥ ከጊዜያዊ የእርስ በእርስ ግጭቶች አልፎ የአንድን ብሄር/ብሄረሰብ አባላት የተወሰነ ሃይማኖትና ባህልና እምነት ተከታዮችን ዒላማ ያደረገ ጅምላ ጥላቻና ጭፍን ጭፍጨፋ ሊካሄድ ያልቻለው:: ይህ ዛሬ ሰልጥነው በከፍተኛ እድገት ደረጃ ላይ ይገኛሉ የሚባሉ ሕዝቦች እንኳ ከታሪካቸው ሊጠቅሱ የማይችሉት የኢትዮጵያዊያን አኩሪ እሴት ምንም እንኳን አልፎ አልፎ አንዳንድ ፈታኝ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ቢቆይም እነሆ ቀጥሎ ይገኛል::

ቀደምት አፄያዊ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዞችም ሆኑ የቅርቡ ወታደራዊ አምባገነንና ጨካኝ አስተዳደር እገሌ ተእገሌ በማይል መንገድ ሁሉንም ህዝቦች ለብዝበዛና አስከፊ ለሆነ የሰብአዊ መብት ረገጣ በተከታታይ መዳረጋቸውና ለተዋራጅነት ህላዌ ማጋለጣቸው ግልጽ ነው:: እነዚህ ኃይሎች በህዝብ ደምና እንባ የራሳቸውንና የመሰሎቻቸውን የተደላደለ የቅምጥል ኑሮ ለማመቻቸትና በቀጣይነትም በሕዝቦች ጫንቃ ላይ እንደሰፈሩ ለመቆየት ባደረጓቸው ጥረቶች የሚመቻቸውን ክፍል በወገንነትና ደጋፊነት ተቀናቃኙን በባዕድነትና በጠላትነት እየፈረጁ የመከፋፈልና የማለያየት ተግባራትን ሲፈጽሙ ኖረዋል:: በሂደቱም በተከናወኑት ማመሰቃቀሎች በተለያየ ደረጃ በህዝቦች ላይ መዘዙ እስካሁንም ሊጠፋ ያልቻለ የታሪክና የሥነ ልቡና ጠባሳ ትተው አልፈዋል::

እነዚህን የተለያዩ ገጽታዎችን የተላበሱ መዛባቶችን ያስተካክላል፡ ለዕድገትና ለብልጽግና እንዲሁም ለሰብአዊ መብቶች መከበር አስተማማኝ ፈር ይቀይሳል ተብሎ ትልቅ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው የ**1966**ቱ ሕዝባዊ የለውጥ እንቅስቃሴም በወታደራዊው አምባገነን ቡድን ተቀልብሶ ሀገሪቱንና ህዝቦቿን ለከፋ ጉስቁልናና ድህነት እንዲሁም ለመራራ የእርስ በእርስ ጦርነት አጋልጦ የድርሻውን ጥፋትና ውድመት ፈጽሞ በህዝቦች ትግል በውርደት ተሰናብቷል:: ወታደራዊው መንግሥት በቀቢፀ ተስፋ ህዝባችንን አለያይቶ ለማፋጀትና ዕድሜውን ለማራዘም ያደረገው ሙከራም በኢትዮጵያዊያን እምቢተኝነት ሳይሰምር ቀርቶ በብዙዎች ዘንድ የተፈራው መጠነ ሰፊ የእርስ በእርስ ፍጅትና የሕዝብ እልቂት ሊገታ ችሏል:: በዚህም የኢትዮጵያዊያን ሰብአዊነትና ጨዋነት እንዲሁም የሥነ ምግባር ባለቤትነት እንደገና ገሀድ ሊሆን ችሏል:: ይህንን አርአያነት የተላበሰ አኩሪ አቋምና የባህርይ መገለጫ ሁላችንም ያለማመንታት ልንኮራበት ይገባል::

በአንፃሩ ግን በአካባቢያችንም ሆነ በአፍሪቃ አህጉር ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ ሀገሮች እንዲሁም ራቅ ባሉት አንዳንድ የዓለም ክፍሎች በጽንፈኛ ርዕዮተዓለምና በአክራሪ ፀረ ዲሞክራቲክ ትምክህተኛና ጠባብ ብሔረተኝነት መነሻነት የተከናወኑ ዘግናኝና አሰቃቂ መናጋቶችና እልቂቶች በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መከሰታቸው ይታወቃል:: ለዚህም በሶማሊያ: በሩዋንዳ: በቡሩንዲና በቦስኒያ የተፈፀሙትን ክንውኖች እንደምሳሌ ማየቱ ይበቃል::

ምንም እንኳን ይህ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ውስጥ ስር ሰዶና የድጋፍ መሠረት ይዞ ጎልቶ ያልወጣ ቢሆንም አንዳንድ ጤናማ ያልሆኑና በቸልታ ከታዩ ጎልብተው መጠነ ሰፊ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ፍንጮች ፈጽሞ አልታዩም ማለት ያዳግታል:: የቡድንና የስብሰቦችን ራስ ወዳድ የሥልጣንና ሌሎች ፍላጎቶችን ለማስፈጸም የነበሩና አሁንም ያሉ መለስተኛ ቅራኔዎችን እያጎሉ በማክረር ውሱን ግቦችን እውን ለማድረግ የሚካሄዱ ሙከራዎች መኖራቸው የአደባባይ ምስጢር ከሆነ ውሎ አድሯል:: በጅምላ አንድን ህዝብ ወይም የህብረተሰብ ክፍል በደለኛና የቀድሞ ወይም የአሁን ጊዜ ተጠቃሚ በማስመሰልና በጠላትነት በመፈረጅ በአንፃሩም ሌላውን በጅምላ የግፍና የመከራ የስቃይና የሰቆቃ ተሸካሚ አድርጎ በማቅረብ ዒላማ በተደረጉ የተወሰኑ ብሔሮች አባሎች ላይ እንዲነሣሣ የሚደረገው ቅስቀሳና ግፊት በቀላሉ መታየት የለበትም:: ዘግናኝ እልቂቶችና ፍጅቶች የተካሄዱባቸውን ሀገሮች ታሪክ በምንመረምርበት ወቅት የምንረዳው አንድ ሐቅ ቢኖር ዘርን: ሃይማኖትንና ሌሎች ቁንጽል ልዩነቶችን ተመርኩዘው የሚነሱ ነውጠኛና ፀረ ዴሞክራቲክ አክራሪ እንቅስቃሴዎችም ሆኑ የጥፋት መልዕክተኞቻቸውና ሐሳዊ መሲሆቻቸው እኩይ ድርጊቶቻቸውን ጀምረው ለፍፃሜ ያደረሱት "የት ይደርሳሉ? ምን ድጋፍ ያገኛሉ?" እየተባሉ ከጥንስሱ በንቀት ስለታለፉ ነው:: የነሂትለር አረመኔነት: የሩዋንዳ ጨፍጫፊዎች ኢሰብአዊነትና የቦስኒያ አክራሪዎች ድርጊት በአስደንጋጭና ዘግናኝ መልኮቻቸው ተግባራዊ መግለጫ ሊያገኙ የቻሉት እንደ ዱብ ዕዳ ወርደውና ደራሽ የውሃ ሙላትን ተመስለው አይደለም:: በቸልታ ሲታለፉ እኔን እስካልነኩ ምንቸገረኝ ሲባሉ ሌላውን በማዳከም እነርሱ ሲጎለብቱ ቀስ በቀስና ደረጃ በደረጃ ጎልምሰው ለሰው ልጆች ሁሉ የሰቆቃና የዋይታ መንስኤ ለመሆን በመብቃት ነው::

በእርግጥ እነዚህን ዘግናኝና አስፈሪ አዝማሚያዎች ብቻ በማጉላትና በማስተጋባት ብቻ ተገቢ ምላሽና ፍትሐዊ መፍትሔ የሚሹ ተገቢና ዴሞክራሲያዊ ይዘት ያላቸው የሕዝብ ጥያቄዎችና የህብረተሰብ ፍላጎቶች ሳይሟሉ አስተማማኝ መረጋጋትና ሰላም ይኖራል ማለት ያዳግታል:: ዳሩ ግን ሕዝቦች ተዋውቀውና ተቀራርበው እነዚህን ጥያቄዎች በጋራ ለመመለስና ችግሮችን ለመፍታት ይችሉ ዘንድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት አላስፈላጊ የሆኑ መናጋቶችንና ምስቅልቅሎችን ማስቀረት ይቻላል የሚል ጽኑ አቋም አለን:: መሠረታዊ የሰው ልጅ መብቶችን ለማስከበር

ፍትሐዊ የህብረተሰብ ሥርዓት የሚሰፍንበትን ጥርጊያ ለማስናዳት በፍቅርና በመተሳሰብ ተከባብሮ በእኩልነት እየኖሩ ለጋራ ዕድገትና ብልጽግና ለመሥራት ከጦርነትና ከጥላቻ ፖለቲካ በመለስ የተለያዩ አማራጮች አሉ ብለን ስለምናምን ይህንን "ወንድማማች ሕዝቦች" የተሰኘውን የሲቪክ ድርጅት ለማቋቋምና ድርጅቱም ሕጋዊ እውቅናን አግኝቶ በይፋ እንዲንቀሳቀስ ተስማምተናል:: ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በጉባዔው ላይ የተገኘነው መሥራቾች በዴሞክራሲያዊ መንገድ በምንመርጣቸው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት አማካይነት ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ሕጋዊ እውቅና እንዲጠይቅ ወስነናል::

## ድ ር ጅ ቱ

"ወንድማማች ሕዝቦች" መንግሥታዊ ያልሆነ: በንግድ ያልተሰማራና ለትርፍ የማይሠራ ከማንኛውም የፖለቲካ: የኃይማኖት ዘርፍ: የብሔር ብሔረሰብ ስብስብና የሙያ ማህበር ያልወገነ ህዝባዊ ድርጅት ነው:: በመሆኑም የዘር: የኃይማኖት የጾታና ሌሎችንም ልዩነቶች ሳያስተናግድ ኢትዮጵያዊያንን የሚያሰባስብ ነው:: ድርጅቱ የሀገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በመንግሥት ታውቆና ተመዝግቦ በይፋና በሰላማዊ መንገድ ዓላማውን በግልጽ ለማራመድ ይንቀሳቀሳል:: መሠረታዊ ዓላማዎቹን የሚቀበሉና ለተግባራዊነቱም የሚታገሉ አባላትና ደጋፊዎችን በማሰባሰብ የሀገሪቱ ሕግና የድርጅቱ ደንብ በሚፈቅዱት መሠረት የተቋቋመበትን ግብ ለመምታት ህጋዊ ፈቃድ እንደተገኘ ሥራውን ይጀምራል:: የድርጅቱ ህገ ደንብ በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ ተረቆ በአባላት ከፀደቀ በኃላ የድርጅቱ መተዳደሪያ ሆኖ ያገለግላል:: የማህበሩ አባላት ሊሆኑ የሚችሉት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ፈቃደኛ ኢትዮጵያዊያን ናቸው:: ሆኖም የድርጅቱን ዓላማ የሚያግዙና ተቀብለው የሚያራምዱ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች ወደፊት የሚወጡ መመዘኛዎችን እስካሟሉ ድረስ በደጋፊነትም ሆነ በተባባሪነት ሊመዘገቡ ይቻላቸዋል::

## የድርጅቱ ዓላማ

ሀ/ የኢትዮጵያ ህዝቦች በመካከላቸው መሠረታዊ ቅራኔ የሌለና በረዥም ዘመን የአብሮ መኖር ታሪካቸው ሰፊ ትስስርና የዳበረ የጋራ ተመክሮ እንዳላቸው በጥንታዊ መረጃ የተደገፈ ትምህርትና ቅስቀሳ ማካሄድ:

ለ/ ለፍትህ: ለሰላም: ለዴሞክራሲና ለጋራ ዕድገትና ብልጽግና ከቆሙ ኃይሎች ጋር በመተባበር በሚቻለው ሁሉ ጥረታቸውን ማገዝ:

ሐ/ ጎጂ ግለኛ ዓላማና ግብን ለማስፈፀም በሕዝቦች መካከል መለያየትንና ግጭትን የሚያራምዱ ከየትኛውም አቅጣጫ የሚነሱ አዝማሚያዎችን ማጋለጥና ከሰላምና ዴሞክራሲ ኃይሎች ጎን በመሆን በሰላማዊ መንገድ መቋቋም:

መ/ ለፍትህ: ለእኩልነትና ለህግ የበላይነት አጋዥ የሆኑ ሁኔታዎችን የሚያራምዱ ተቋማትና ኃይሎች በተሳካ ሁኔታ እንዲሰፍኑ የተቻለውን እገዛ ሁሉ ማድረግ:

ሠ/ ከብሔር ብሔረሰቦች የተውጣጡ የሀገር ሽማግሌዎች: ምሁራን: የፖለቲካ መሪዎች: የልዩ ልዩ ኃይማኖቶች መሪዎች: የወጣትና የሴቶች ማህበራት ተወካዮች: ተመራማሪዎችና የታሪክ አዋቂዎች ... ወዘተ በየጊዜው እየተገናኙ ሃሳብ የሚለዋወጡባቸው: ልምዳቸውንና ዕውቀታቸውን የሚያካፍሉባቸው: ሃሳቦችን የሚያመነጩባቸው: ችግሮችን አቅርበው የሚወያዩባቸውና የመፍትሔ ሃሣብ የሚሰነዝሩባቸው የጋራ መድረኮች በሀገር አቀፍና እንዳስፈላጊነቱ በክልሎች እንዲዋቀሩ ማድረግ:

ረ/ የሀገሪቱንና የሕዝቦቿን ታሪክ በተመለከተ በነባራዊ እውነታዎች ላይ የተመረኮዘና ከአድላዊ ወገናዊነትና ከስሜታዊነት በፀዳ ሁኔታ ምርምርና ጥናት እንዲካሄድ ማገዝና ማበረታታት: የጥናት ውጤቶችም ባልተዛባና አግባብ ባለው ሁኔታ በልዩ ልዩ መንገድ ለህዝብ እንዲሰራጩ ማድረግ:

ሰ/ የድርጅቱን መሠረታዊ ዓላማዎች ማለትም የኢትዮጵያን ሕዝቦች ወንድማማችነት፡ የፍትህ የሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነትን መስፈን አስፈላጊነት፡ ለጋራ፡ ዕድገትና ብልጽግና በህብረት የመሥራትን ጠቃሚነት የሚያንፀባርቁ ግንዛቤዎችን በመንግሥትና በግል የመገናኛ ብዙኃን አማካይነት በህዝብ ውስጥ እንዲሰርፁ ቅስቀሳና ትምህርት መስጠት፡

ሸ/ በተለያዩ አካባቢዎች በሕዝቦች መካከል ቅራኔዎችና ግጭቶች ሲከሰቱ ጉዳት ከመድረሱና ነገሩ ከመባባሱ በፊት በስፍራው በመገኘትና ሁኔታዎችን በማጥናት ጉዳዮች በሰላም የሚያልቁበትን መንገድ በመሻት የመፍትሔ ሃሳቦችን ለመንግሥትና ለሚመለከታቸው ወገኖች በማቅረብ የመከላከል ዲፕሎማሲ (preventive diplomacy) ሚና መጫወት፡

ቀ/ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የወል ተመክሮዎችንና የህብረተሰብ ሕይወት የሚገልፁ የታሪክና የባህል እሴቶች ተሰብስበውና ተደራጅተው በጋራ ቅርስነት ለትውልድ የሚተላለፉበትን ሁኔታ የሚያመቻቹ ተቋማትና ድርጅቶችን ማገዝ፡፡

እኛ ስማችንና አድራሻችን ከዚህ በታች የተጠቀሰው የወንድማማች ሕዝቦች ድርጅት መሥራች አባሎች መሆናችንን በፊርማችን እናረጋግጣለን::

| ተራ ቁጥር | ስም | አድረሻ | ብሔር/ብሔረሰብ | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዳንኤል መለኩ | አ/አበባ | ትግሬ | |
| 2 | ደነቢ ገሩሙ | " | ኦሮሞ | |
| 3 | ማጀረ ተከሰተ | " | ትግሬ | |
| 4 | ታምራት ማንተጋፍቶ | " | አማራ | |
| 5 | አበበች እንዳለ | " | አማራ | |
| 6 | ብርሃኑ ወ/ሰንበት | " | ኦሮሞ | |
| 7 | ደረጀ ኃይሉ | " | አማራ | |
| 8 | አሥራት አንለይ | " | አማራ | |
| 9 | ፀጋዬ ወልዴ | " | ኦሮሞ | |
| 10 | እንድሪያስ ቴኒ | " | ጉራጌ | |
| 11 | ደምሴ ሥዩም | ደቡብ ኢትዮጵያ | ሀዲያ | |
| 12 | ሞገስ አወቀ | አ/አበባ | አማራ | |
| 13 | ገብረየስ አለማየሁ | " | የም | |
| 14 | ማሞ ወጌጋ | " | ጌዶአ | |
| 15 | እውነቱ ደፈርሻ | " | ጋሞ | |
| 16 | ተክሌ ሸለጌቶ | " | ከፋቾ | |
| 17 | ምትኬ ገዳ | " | ጉራጌ | |
| 18 | ቢንያም ሄራጎ | " | ጠምባሮ | |
| 19 | አንተነህ መርዕድ | " | አገው | |
| 20 | ጴጥሮስ ኪያ | " | የም | |